ቁ/ዐመ6ዐ0/4
9/01/2011

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development & Housing

751/2013

ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
<u>ከ/ል/ቤ/ሚ</u>

ጉዳዩ፡ <u>የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ</u>

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የከተሞች ራስን የማስተዋወቅ ውድድር ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 63/2011 ሆኖ ከመስከረም 8 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን የጸደቀ በመሆኑ የመመሪያውን ተፈጻሚነት እንድትከታተሉና እንድታስፈጽሙ የጸደቀውን 1 ጥራዝ መመሪያ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር
ኢንጂነር አባይ ይግዛው
ሚኒስትር

ግልባጭ፡-
- ለክብርት ሚኒስትር ዴኤታ ( የከተማ ልማት ዘርፍ)፣
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ( የቤቶችና መሠረተ ልማት ዘርፍ)፣
- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና ሚኒ ካቢኔጉዳዮች ቢሮ
- ለሕግ ዳይሬክቶሬት
  <u>ከ/ል/ቤ/ሚ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT & HOUSING

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም
Ethiopian Urban Forum

# የከተሞች ራስን የማስተዋወቅ ውድድር ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 751/2013

መስከረም 2011 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ፈጣን የከተሞች መስፋፋትን ተከትሎ የከተማ ነዋሪዎችንና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማጠናከር መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በማስፋፋት የከተማ ልማት ፖሊሲ እንዲሁም ፖሊሲውን መነሻ ተደርገው የተዘጋጁ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ትግበራና ስኬት ማፋጠን ይቻል ዘንድ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በተለያዩ ከተሞች አስተናጋጅነት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚከበር በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ከተሞች በአሁኑ ወቅት በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ከፍተኛ እድገት እያስመዘገቡ እና ለአገራዊ ምጣኔ ሃብት ዕድገት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እያደገ የመጣ ስለሆነ ከተሞች የልማት ሥራዎቻቸውን የሚያሳዩበት፣ እርስ በእርስ የሚማማሩበት፣ ለነዋሪዎቻቸው እና ለባለድርሻ አካላት አስፈላጊ መረጃ የሚሰጡበት፣ እንዲሁም የኢንቨስትመንት፣ የቱሪዝም፣ የገበያና የሌሎች መስህቦቻቸውን የሚያስተዋውቁበት የከተሞች እራሳቸውን የማስተዋወቅ ሥራ (City Marketing) ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በአገር-አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በማካሄድ ከተሞችን እርስ በእርስ በማወዳደር ዕውቅና እና ሽልማት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የከተሞች እራሳቸውን የማስተዋወቅ ውድድሩን ግልጽ፣ ፍትሃዊ እና በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል መስፈርት በማዘጋጀት መምራት የሚገባ በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 26 የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት በአግባቡ ለመተግበር ይችል ዘንድ ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የከተሞች ራስን የማስተዋወቅ ውድድር ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 751/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) «ከተማ» ማለት የህዝብ ቁጥራቸው ከ2000 በላይ የሆነ እና በከተሞች ፎረም ተሳታፊ የሆኑ ከተሞች ማለት ነው፡፡

2) «ከተማን ማስተዋወቅ» ማለት ከተሞች በአስሩ አምዶች የሰሯቸውን ስራዎች እና ለኢንቨስትመንት ያሳቸውን አማራጮች ለከተማው ህዝብና ለልማት አጋሮቻቸው መረጃ በመስጠት ራሳቸውን ማስተዋወቅ ማለት ነው፡፡

3) «ምድብ» ማለት ለዚህ ውድድር ሲባል ከተሞች በተለያየ ምድብ ተከፋፍለው የሚወዳደሩበት ምደባ ማለት ነው፡፡

4) «ዳኞች» ማለት ለዚህ ውድድር ሲባል በዓብይ ኮሚቴ የሚሰየሙ የከተሞች ራስን የማስተዋወቅ ውድድር የሚዳኙ ኃላፊዎች ወይም ባለሞያዎች ናቸው፡፡

5) «መረጃ» ማለት በውድድሩ ጊዜ ከተሞች ራሳቸውን ለማስተዋወቅ የሚያቀርቡት የፅሁፍ፣ የቻርቶች፣ የፎቶ ግራፎች እንዲሁም ሌሎች ተንቀሳቃሽ ፊልሞችንና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል መግለጫ ማለት ነው፡፡

6) «ሚኒስቴር» ማለት የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ነው፣

7) «ክልሎች» ማለት በኢትዮጵያ ፌ/ዲ/ሪ/ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡

8) «የከተሞች ፎረም» ማለት በከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ አጀንዳዎች ዙሪያ ጠንካራ መሰረት ያለዉ የከተማ ህዝብ ንቅናቄና ተጠቃሚነት ለመፍጠር እንዲቻል በየሁለት ዓመቱ የሚከበር የኢትዮጵያ ከተሞች በአል ነው፡፡

9) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## 3. የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በየሁለት ዓመቱ የሚካሄደውን የኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም (በዓል) እንዲዘጋጅ በሚወሰንለት ከተማ እንደአስፈላጊነቱ በአራት እና ከዛም በላይ በሆነ ምድብ ተከፋፍለው የራስን የማስተዋወቅ ውድድር ላይ በሚሳተፉ ከተሞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 4. የመመሪያው ዓላማ

ከተሞች የልማት ሥራዎቻቸውን የሚያሳዩበት፣ እርስ-በእርስ የሚማማሩበት፣ ለነዋሪዎቻቸው እና ለባለድርሻ አካላት አስፈላጊ መረጃ የሚሰጡበት፣ እንዲሁም የኢንቨስትመንት፣ የቱሪዝም፣ የገበያና የሌሎች መስህቦቻቸውን የሚያስተዋውቁበት ውድድርን ፍትሃዊ በሆነ የከተሞች ምድብ ለማከናወን እና ውድድሩን ከአድሎ የነፃ፣ ከተሞች ባቀረቡት ራስን የማስተዋወቅ ስልትና ጥረት ልክ ለመምራት ነው።

## ክፍል ሁለት

## የከተሞች ራስን ማስተዋወቅ ውድድር

### 5. የውድድር ምድቦች

1) የኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም ተወዳዳሪ ከተሞች እንደአስፈላጊነቱ በአራት እና ከዛም በላይ በሆነ ምድብ ይወዳደራሉ፣
2) ውድድሩን ፍትሃዊ ለማድረግ የከተሞች መሠረተ-ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (ULGDP) ተሳታፊ ከተሞች ከሌሎች በተለየ ምድብ ይወዳደራሉ፣
3) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም ተሳታፊ ከተሞች የራሳቸውን እህት ከተማ እንዲሳተፍ የሚያደርጉ ከሆነ በልዩ ተሳታፊነት ዕውቅና እንዲያገኙ ይደረጋል፣
4) የከተሞች ምድብ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

| ተ.ቁ | ምድብ | የህዝብ ብዛታቸው | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| 1 | ምድብ አንድ | 18 የULGDP - I ተጠቃሚ ከተሞች | |
| 2 | ምድብ ሁለት | 26 የULGDP - II ተጠቃሚ ከተሞች | |
| 3 | ምድብ ሦስት | 20,000 እና በላይ የህዝብ ብዛት ያላቸው ከተሞች | |
| 4 | ምድብ አራት | ከ2,000 - 19,999 የህዝብ ብዛት ያላቸው ከተሞች | |
| | አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር | | በልዩ ሁኔታ ተሳታፊ ከተማ |
| | እህት ከተሞች | | በልዩ ሁኔታ ተሳታፊ ከተሞች |

### 6. የውድድር ይዘት

1) **በውድድሩ የሚካተቱ የከተሞች እራስን የማስተዋወቅ የትኩረት ነጥቦች**

ከተሞች ራስን ለማስተዋወቅ ውድድር መነሻ የሚደርጉት በዘርፉ የተለዩትን ምሰሶዎች (Pillars) ሆኖ ባለፉት ሁለት የበጀት ዓመታት ከእነዚህ ምሰሶዎች አንጻር ያከናወኗቸውን ሥራዎች አፈፃፀም ብቻ ለህዝብ እና ለልማት አጋሮች ማሳወቅን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፣ ምሰሶዎች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

ሀ) የከተሞች አመራር ልማት አቅም ግንባታ፣

ለ) የከተሞች የሥራ እድል ፈጠራ፣

ሐ) የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ፣

መ) የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ፣

ሠ) የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት፣

ረ) የከተማ እና የገጠር መኖሪያ ቤት ልማት፣

ሰ) የከተሞች የተቀናጀ መሰረተ-ልማት አቅርቦት፣

* የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር * ሪከርድና ማህደር

ሸ) የከተሞች ፅዳት፣ አረንጓዴ ልማት፣

ቀ) የከተሞች ገቢና ፋይናስ ልማት፣ እና

በ) ተደራሽና የሕዝቡን ደህንነት የሚያረጋግጥ የከተማ ልማት ሥራዎች ናቸው፡፡

2) በውድድሩ የሚቀርቡ መረጃዎች ይዘት

ሀ) የከተሞች አመራር ልማት አቅም ግንባታ ሥራዎች አፈጻጸም፣

ለ) የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎች አፈጻጸም፣

ሐ) የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ሥራዎች አፈጻጸም፣

መ) የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ሥራዎች አፈጻጸም፣

ሠ) የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች አፈጻጸም፣

ረ) የከተማ ቤት ልማትና አስተዳደር ሥራዎች አፈጻጸም፣

ሰ) የከተሞች የተቀናጀ የመሠረተ-ልማት አቅርቦት ሥራዎች አፈጻጸም፣

ሸ) የከተሞች ፅዳት፣ አረንጓዴ ልማት ሥራዎች አፈጻጸም፣

ቀ) የከተሞች ገቢና ፋይናንስ ልማት ሥራዎች አፈጻጸም፣

በ) ተደራሽና የሕዝቡን ደህንነት የሚያረጋግጥ የከተማ ልማት ሥራዎች አፈጻጸም፣

ተ) ለኢንቨስትመንት የተዘጋጁ ምቹ ሁኔታዎች መረጃ፣

ቸ) የነዋሪው ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት የሚያመላክቱ መረጃዎች፣

ነ) የቱሪዝም መስህቦችን እና ታሪካዊ መረጃዎችን ያካተቱ መሆን የሚገባቸው ሲሆን ከዚህ ከተዘረዘሩት የመረጃ ዓይነቶች ውጪ የሚቀርቡ መረጃዎች በማወዳደሪያ መስፈርትነት አያገለግሉም፡፡

3) የመረጃ ዝግጅትና አቀራረብ

ሀ) በጽሑፍ የሚቀርቡ መረጃዎች በግልጽ የሚነበቡ እና ግድፈት የሌለባቸው መሆን አለባቸው፣ በተጨማሪም በእጅ ያልተጻፉ እና ባለቀለም መሆን አለባቸው፣

ለ) የመረጃ ቻርቶች ባለቀለም፣ በግልጽ የሚታዩ፣ በእጅ ያልተዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል፣ በሚታይ ሁኔታ መስቀል አለባቸው፣ የቻርቶቹ መጠን ከA3 መጠን ያላነሰ መሆን አለበት፤

ሐ) ፎቶግራፎች በጥራት የተነሱ ገላጭ እና ለእይታ አመቺ መጠን ያላቸው መሆን ይገባቸዋል፣ ለኤግዚቢሽን የሚቀርቡ የፎቶግራፎች መጠን ከA4 መጠን ያላነሰ መሆን አለበት፤

4) ለጎብኚዎች የሚደረግ ገለጻ

ሀ) ጎብኚዎችን ለመሳብ የተለያዩ ዘዴዎች /ቻርቶች፣ ጽሁፎች እና ፎቶ-ግራፎች/፣ ኦዲቪዥዋል በመጠቀም መቅረብ ይኖርበታል፤

ለ) አጠር ባለ ጊዜ ውስጥ ከ5 -10 ደቂቃ በቂ መረጃ መስጠት ይኖርበታል፤

5) የድምፅ አጠቃቀም

ሀ) ኤግዚቢሽኑን ብሎም ሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ዝግጅቶችን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ይቻል ዘንድ የበዓሉ ቦታ ለመደማመጥና መግለጫዎችን በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት የሚያስች የድምፅ አጠቃቀም መኖር አለበት፣

ለ) ተሳታፊዎች የሚጠቀሙባቸው እንደ ሙዚቃ፣ የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች፣ ፊልሞች፣ መግለጫዎች ወዘተ... የመሳሰሉት ድምፅ በአካባቢያቸው ያሉትን ሌሎች ተሳታፊዎች በማያውክ ሁኔታ ከ60 DB መብለጥ የለበትም፤

6) የውድድሩ እና የዳኝነት ሂደት

ሀ) የዳኞች ቡድን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 በተቀመጠው መስፈርት መሠረት በዓብይ ኮሚቴ ይሰየማሉ፤

ለ) የከተሞች ራስን ማስተዋወቅ ዝግጅትን ለማወዳደር ለተመረጡ ዳኞች ገለጻ ይደረጋል፤

ሐ) የዳኞች ቡድን አባላቱ በውድድር መስፈርቶች ላይ በመወያየት የጋራ ግንዛቤ ይይዛሉ፤ የውድድሩ መስፈረቶችና ለየመስፈርቱ የሚሰጠው ከፍተኛ ነጥብ በዚህ የውድድር መመሪያ ላይ የተገለጸው ይሆናል፤

መ) የዳኞች ቡድን የየራሳቸውን ሰብሳቢና ፀሐፊ ይኖራቸዋል፣ ሰብሳቢዎቹም በቀጣይ የዳኞች ቡድን የሚያደርጉዋቸውን ስብሰባዎች እንዲሁም የውድድሩን ሂደት ይመራሉ፣

ሠ) የዳኞች ቡድን ከኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም መክፈቻ ጀምሮ በበዓሉ አከባበር ወቅት የተሳታፊ ከተሞች ኤግዚቢሽን እየተዘዋወሩ ይጎበኛሉ፣ ሆኖም የጉብኝት ኘሮግራም በከተሞቹ መታወቅ የለበትም፤

ረ) የዳኞች አባላት እንደ ስምምነታቸው በጋራ ወይም በተናጥል የከተሞችን ዝግጅት ሊጎበኙ ይችላሉ፤

ሰ) አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የውድድር ምድቦችን በንዑስ ቡድን በመክፈል የዳኝነት ሂደቱ ሊካሄድ ይችላል፤ ውጤቱ የሚወሰነው የንዑሳን ቡድኖች አማካኝ ውጤት በመውሰድ ይሆናል፤

ሸ) የዳኞች ቡድን አባላት በየእለቱ ማጠቃለያ እየተገናኙ ስለቀኑ ውሎአቸው፣ በእለቱ ስለሰጡዋቸው ነጥቦች እና ነጥቦቹን ስለሰጡበት ምክንያት እንዲሁም ስለውድድሩ አጠቃላይ ሂደት ይወያያሉ፤

ቀ) በአባላት መሃከል የሀሳብ ልዩነት ቢፈጠር በተቻለ መጠን ለማግባባት ሙከራ ይደረጋል፤ ካልሆነ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፤

በ) በኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ማጠቃለያ ዋዜማ የዳኞች ቡድን አባላት በየቡድናቸው ይገኛሉ፣ እያንዳንዱ አባል ለገመገመው ከተማ የሰጠውን ውጤት በውጤት መመዝገቢያው ላይ በግልጽ

በመጻፍ እና በአባሪ-3 ላይ ፎ[illegible]ፈር ያስረክባል፤

ተ) የዳኞች አማካይ ውጤት ተደምሮ ከፍተኛውን ውጤት (ከ1ኛ - 3ኛ) ያገኙ ከተሞች ይለያሉ፣ በውጤቱ ላይም የዳኞች ቡድን አባላቱ አስተያየቶቻቸውን ተለዋውጠው የጋራ መግባባት ላይ ይደርሳሉ፤

ቸ) የከተሞች የዕርስ በርስ ውድድር ማጠቃለያ ውጤት ይፋ ከመደረጉ በፊት በዓብይ ኮሚቴ መጽደቅ ይኖርበታል፣

ነ) እያንዳንዱ ቡድን የውድድሩ አሸናፊዎችን የሚገልጽ ቃለ-ጉባኤ አዘጋጅቶ የሚያቀርብ ሲሆን በተጨማሪም በከተሞች ኤግዚቢሽን እና ከተማን የማስተዋወቅ ሥራ የታዘቡዋቸውን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች እንዲሁም የማሻሻያ ሀሳቦችን በሪፖርት መልክ ማዘጋጀት ይጠበቃል፣ ይህ ሪፖርትም ከውድድሩ ማብቂያ በኋላ ለተሳታፊ ከተሞች የሚሰጥ ግብረ-መልስ ይሆናል፤

ኘ) የዳኞች ቡድን አሸናፊዎች በይፋ ታውቀው ሽልማት እስከሚቀበሉበት የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም መዝጊያ ሥነ-ስርዓት ድረስ የውድድሩን ውጤት በሚስጥር ይይዛሉ፤

ኸ) ለአሸናፊ ከተሞች ሽልማት ከተሰጠ በኋላ የውድድርና ሽልማት ንኡስ ኮሚቴው እና ዳኞች በተገኙበት በውድድሩ አጠቃላይ ሂደት እና መሻሻል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ግምገማ ይካሄዳል።

## 7. የዳኞች ምልመላ ሂደት እና መስፈርት

1) ዳኞች ከሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከፌዴራል ተጠሪ ተቋማት እና ሌሎች ሚኒስቴር መ/ቤቶች አመራሮች እና ባለሙያዎች ሊመለመል የሚገባ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ከሚዲያ እና ከትምህርት ዘርፍ ባለሙያዎች ሊካተቱ ይችላል፣

2) በዳኝነት የተሰየሙት አመራሮች እና ባለሙያዎች ማንነታቸው እስከ ውድድሩ ማጠቃለያ ድረስ በይፋ አይገለጽም፤

3) የዳኞች የመመልመያ መስፈርቶች፡-

ሀ) በዘርፉ ላይ በቂ እውቀት እና ልምድ ያላቸው፣

ለ) መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸው፣

ሐ) ኃላፊነትን በብቃት መወጣት የሚችሉ፣

መ) በታማኝነታቸው እና በእውነተኛነታቸው የተመሰከረላቸው፣ እና

ሠ) ከዚህ ቀደም በተካሄዱ የከተሞች ራስን የማስተዋወቅ ውድድሮች ላይ የመሳተፍ ልምድ ያላቸው እና ኃላፊነታቸውን በብቃት የተወጡ ናቸው።

4) በዳኝነት ከተሰየሙት አመራሮች እና ባለሙያዎች መካከል የተሰጣቸውን ኃላፊነት በታማኝነት፣ በቅንነትና ህግን አክብረው የማያከናውኑ ከተገኙ በዲሲፒሊን ተጠያቂ ይሆናሉ፤

## 8. የከተሞች ራስን የማስተዋወቅ ውድድር መስፈርቶች

| ተ.ቁ | የውድድሩ መስፈርት | የሚሰ ከፍተኛ |
|---|---|---|
| 8.1 | **የጎብኝዎች አቀባበል እና ገለፃ** | 18 |
| 8.1.1 | የገለጻ ሰጪዎች በቦታ መገኘት | 2 |
| 1) | ገለጻ ሰጪዎች መለያ ባጅ አድርገው በቦታው የተገኙ ከሆነ | 2 |
| 2) | ገለጻ ሰጪዎች መለያ ባጅ ሳያደርጉ በቦታው የተገኙ ከሆነ | 1 |
| 3) | ገለጻ ሰጪዎች በቦታው ያልተገኙ ከሆነ | 0 |
| 8.1.2 | ገለፃው የፈጀው ጊዜ (በአጭር ጊዜ በቂ መግለጫ መስጠት መቻል) | 1 |
| 1) | ገለጻው ከ5 ደቂቃ በታች የፈጀ ከሆነ | 1 |
| 2) | ገለጻው ከ5-10 ደቂቃ የፈጀ ከሆነ | 0.5 |
| 3) | ገለጻው ከ10 ደቂቃ በላይ የፈጀ ከሆነ | 0 |
| 8.1.3 | የገለፃው ይዘት (Relevance) | 3 |
| 1) | የዘርፉን ዋና ዋና ፒላሮች ያካተተ ከሆነ | 2 |
| 2) | የኢንቨስትመንት፣ የቱሪዝም መስህቦችና ታሪካሪ መረጃዎችን ያካተተ ከሆነ | 0.5 |
| 3) | የከተማውን አመሠራረትና እድገት ያካተተ ከሆነ | 0.5 |
| 8.1.4 | ጎብኚዎች ሲደርሱ በቦታው የነበረው (የነበሩት) የከተማ ተወካዮች ያደረጉት አቀባበል (ሰላምታ፣ ፈገግታ፣ ቅልጥፍና፣ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን)፣ ወዘተ | 2 |
| 1) | በቂ አቀባበል የተደረገ ከሆነ | 2 |
| 2) | በቂ አቀባበል ያልተደረገ ከሆነ | 0 |
| 8.1.5 | የድምጽ አጠቃቀሙ ለመደማመጥ እና መግለጫዎችን በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት የሚያስችል እና ሌሎች ተሳታፊዎች የማያውክ ከሆነ | 10 |
| 1) | የድምጽ አጠቃቀሙ ከ60 DB በታች ከሆነ (ለመደማመጥ አስቸጋሪ ያለሆነ) | 10 |
| 2) | የድምጽ አጠቃቀሙ ከ60 DB በላይ ከሆነ (ለመደማመጥ አዳጋች ከሆነ) | 0 |
| 8.2 | **የኤግዚቢሽን አቀራረብ (ከተማው በኤግዚቢሽን መመሪያው የተካተተውን የጥራትና የይዘት መመሪያ መከተሉ)** | 24 |
| 8.2.1 | በውድድሩ የሚቀርቡ መረጃዎች ይዘት | 14 |
| 1) | የዘርፉን ዋና ዋና ምሶሶዎች (Pillars) መረጃ ያካተተ | 11 |
| 2) | ለኢንቨስትመንት የተዘጋጁ ምቹ ሁኔታዎች መረጃ | 1 |
| 3) | የቱሪዝም መስህቦችን እና ታሪካዊ መረጃ | 1 |
| 4) | የነዋሪው ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን መረጃ | 1 |
| 8.2.2 | የቀረቡ መረጃዎች ጥራት | 3 |
| 1) | ጽሑፎችና ቻርቶች በግልጽ የሚነበቡና ሥርዝ ድልዝ የሌለባቸው እና መግለጫዎች ካሏቸው | 2 |
| 2) | የመረጃ ጽሑፎችና ቻርቶች ባለቀለም ከሆኑ | 1 |
| 8.2.3 | የኤግዚቢሽን የአቀራረብ ቅደም ተከተል | 1 |
| 1) | የከተማውን አመሠራረትና እድገት መጀመሪያ የተገለፀ ከሆነ | 1 |
| 2) | የከተማውን አመሠራረትና እድገት ያልተገለጸ ከሆነ | 0 |
| 8.2.4 | የቻርተሮች፣ ፎቶ-ግራፎችና ፊልሞች አጠቃቀም | 3 |
| 1) | ከA3 መጠን ያላነሰ ቻርቶችንና ፎቶ-ግራፎች የተጠቀመ ከሆነ | 2 |
| 2) | ከA3 መጠን በታች ቻርቶችንና ፎቶ-ግራፎች የተጠቀመ ከሆነ | 1 |
| 3) | ዶክሜንቴሪ ፊልሞች የተጠቀመ ከሆነ | 1 |

| ተ.ቁ | የውድድሩ መስፈርት | የሚሰጠው ከፍተኛ ነጥብ |
|---|---|---|
| 4) | ቻርተሮች፣ ፎቶግራፎችና ፊልሞችን ያልተጠቀመ ከሆነ | 0 |
| 2.5 | ኤግዚቢሽኑ የከተማውን የልማት እንቅስቃሴ የኢንቨስትመንት የቱሪዝም መስህቦች በሚገባ ማንፀባረት መቻሉ | 3 |
| 1) | የኢንቨስትመንት፣ የቱሪዝም እና የባህል፣ ቅርስና ታሪካዊ መስህቦች በሙሉ የቀረቡ ከሆነ | 3 |
| 2) | የኢንቨስትመንት መስህቦች ብቻ የቀረቡ ከሆነ | 1 |
| 3) | የቱሪዝም መስህቦች ብቻ የቀረቡ ከሆነ | 1 |
| 4) | የባህል፣ የቅርስ እና ታሪካዊ መስህቦች ብቻ የቀረቡ ከሆነ | 1 |
| 5) | ምንም አይነት መስህቦች ያልተቀረቡ ከሆነ | 0 |
| 3 | ጥቅም ላይ የዋሉ ራስን የማስተዋወቂያ መንገዶች ወይም ጥረቶች | 15 |
| 3.1 | የተዘጋጁ ንግድ ትሪኢቶችና ሴሚናሮችና ጥናታዊ ጉብኝቶች አፈጻጸም ከቀረቡ | 5 |
| 3.2 | ባህላዊ ስፖርታዊ ሁነቶችን ስፖንሰር ማድረግና ማስተናገድ አፈጻጸም ከቀረበ | 5 |
| 3.3 | ከተማው ራሱን በሚዲያ ያስተዋወቀ ከሆነ | 3 |
| 3.4 | ከተማው ራሱን ዌብሳይት በማዘጋጀት ያስተዋወቀ ከሆነ | 2 |
| 4 | የከተማዋ ልዩ መገለጫዎች | 11 |
| .1 | ሎጎ | 3 |
| 1) | ሎጎ ያለው ከሆነ | 3 |
| 2) | ሎጎ የሌለው ከሆነ | 0 |
| .2 | ሲቲ ብራንድ (ልዩ መገለጫ ስም) | 3 |
| 1) | ሲቲ ብራንድ ያለው ከሆነ | 3 |
| 2) | ሲቲ ብራንድ የሌለው ከሆነ | 0 |
| .3 | ለጎብኚዎቹ የሚሰጡ የተለያዩ ብሮሽሮች ተዘጋጅተው ስለመቅረባቸው | 2 |
| 1) | የተለያዩ ብሮሽሮችን ያዘጋጀ ከሆነ | 2 |
| 2) | የተለያዩ ብሮሽሮች ያላዘጋጀ ከሆነ | 0 |
| .4 | ለኤግዚቢሽኑ ድምቀት የሚሰጡ ባህላዊ እሴቶች | 3 |
| 1) | ባህላዊ እሴቶችን ያቀረበ ከሆነ | 3 |
| 2) | ባህላዊ እሴቶች ያላቀረበ ከሆነ | 0 |
| | አዲስ የፈጠራ ውጤት | 7 |
| | የጥ/አ/ኢ/ልማት የሚያፋጥን ግኝት | 3 |
| 1) | ግኝቱ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከሆነ | 3 |
| 2) | ግኝቱ በሌሎች የከተማ ልማት ዘርፍ ዘርፎች ከሆነ | 1 |
| 3) | ምንም ግኝት ያላቀረበ ወይም ከከተማ ልማት ዘርፍ ውጭ የቀረበ ከሆነ | 0 |
| 2 | ለፈጠራ ውጤት እውቅና ለሚመለከተው አካል የተሰጠ ከሆነ | 2 |
| 1) | ፈጠራው በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ሆኖ የፈጠራ ውጤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የተሰጠው እና በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጠው ከሆነ | 2 |
| 2) | ፈጠራው በሌሎች ዘርፍ ሆኖ የፈጠራ ውጤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የተሰጠው እና በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጠው ከሆነ | 1 |
| 3 | የፈጠራ ሥራው የጥሬ ዕቃ አጠቃቀም | 2 |
| 1) | ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ጥሬ እቃ የተጠቀመ ከሆነ | 2 |
| 2) | የሀገር ውስጥ እና የውጭ ጥሬ እቃ የተጠቀመ ከሆነ | 1 |

| .ቁ | የውድድሩ መስፈርት | የሚሰጠው ከፍተኛ ነጥብ |
|---|---|---|
| 3) | ሙሉ በሙሉ ከውጭ ጥሬ እቃ የተጠቀመ ከሆነ | 0 |
| 6 | ከተሞች ኢንቨስተሮችን እና ቱሪስቶችን ለመሳብ፣ ገቢያቸውን ለማሳደግና ለመጠቀም የተደረገ ጥረት፣ | 25 |
| 6.1. | የተዘጋጁ የኢንቨስትመንት አማራጮች፣ ዝግጅ የሆነ የመሬት አቅርቦትና መሰረተ-ልማት | 8 |
| 1) | በጥናት የተደገፈ የኢንቨስትመንት አማራጭ መረጃ መቅረቡ | 3 |
| 2) | በጥናት የተደገፈና ዝግጁ የሆነ መሬት እና መሰረተ-ልማቶች መሟላታቸውን የሚያመላክት መረጃ መቅረቡ | 3 |
| 3) | በጥናት ያልተደገፉ የኢንቨስትመንት አማራጮች እና ዝግጅ የሆነ የመሬት አቅርቦትና መሰረተ-ልማት መረጃዎች ስለመቅረባቸው | 2 |
| .2 | ቱሪስቶች ለመሳብ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች (የሚቀርቡ መረጃዎች በብሮሸር) | 7 |
| 1) | መስህቦችን በመገናኛ ብዙኃን (በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ ወይም በኢንተርኔት) ለማስተዋወቅ የተደረገ ጥረት | 3 |
| 2) | መስህቦችን በመጽሄትና በጋዜጣ ለማስተዋወቅ የተደረገ ጥረት | 2 |
| 3) | መስህቦችን በብሮሸርና በራሪ ወረቀት ለማስተዋወቅ የተደረገ ጥረት | 2 |
| .3 | ከሀገር ውጪ ያሉ የከተማ ነዋሪዎችን (ዳያስፖራ) ተሳትፎ ለማሳደግ የተደረገ ጥረት | 5 |
| 1) | የዲያስፖራው ኮሚኒቲ በከተማው እንዲሳተፍ ልዩ ማበረታቻ መኖሩ | 3 |
| 2) | የኢንቨስትመንት አማራጮችን በተለያዩ ሚዲያዎች እንዲሁም በመድረክ ለዲያስፖራው ኮሚኒቲ ለማስተዋወቅ የተደረገ ጥረት | 2 |
| 4 | በራስ አቅም ገቢ ለማሳደግ የተዘጋጁ ፕሮጀክቶችና የተቀየሱ አማራጮች፣ የተፈጠረ ገቢ ስለመቀረቡ | 5 |
| 1) | ከተሞች ገቢያቸውን ለማሳደግ የተዘጋጁ ፕሮጀክቶችና የተገኘ ገቢ፣ | 3 |
| 2) | ከተሞች ገቢያቸውን ለመጠቀም የተደረገ ጥረትና የተገኘ ውጤት፣ | 2 |
| | **ድምር ውጤት** | 100 |

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 9. የውድድር ጊዜ

የከተሞች ራስን ማስተዋወቅ ውድድር የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም እንዲካሄድ በተወሰነባቸው ቀናት ውስጥ የሚከናወን ይሆናል፡፡

### 10. የእውቅና ሽልማት ዓይነት

በከተሞች የራስ ማስተዋወቅ ውድድር ተሳታፊ ከነበሩት፡-

1) ከየምድቡ 1ኛ ለሚወጣ ከተማ ሰርተፍኬት እና 7x6x1.25 ሳ.ሜ ኢንግሬቨድ ክሪስታል ዋንጫ እና 55 ኢንች ቴሌቪዥን፣
2) ከየምድቡ 2ኛ ለሚወጣ ከተማ ሰርተፍኬት እና 6x4x1.25 ሳ.ሜ ኢንግሬቨድ ክሪስታል ዋንጫ እና 42 ኢንች ቴሌቪዥን፣
3) ከየምድቡ 3ኛ ለሚወጣ ከተማ ሰርተፍኬት እና 4x4x1.25 ሳ.ሜ ኢንግሬቨድ ክሪስታል ዋንጫ እና 32 ኢንች ቴሌቪዥን፣
4) ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰርተፍኬት እና ልዩ ዋንጫ በልዩ ተሳታፊነት፣
5) ለእህት ከተሞች ሰርተፍኬትና ልዩ ዋንጫ በልዩ ተሳታፊነት፣ እና
6) በውድድሩ ለተሳተፉ ሁሉም ከተሞች የተሳትፎ የምስክር ወረቀት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

### 11. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 12. ከመመሪያው ጋር የሚቃረን መመሪያ ወይም አሰራር

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

### 13. መመሪያው የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ ከ[illegible] 07 [illegible] 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ጀንጥራር አባይ

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር

## አባሪዎች

### አባሪ 1፡- የየዕለቱ የውጤት መሙያ ስንጠረዥ

| ተ.ቁ | የውድድሩ መስፈርት | ከተማ 1 | ከተማ 2 | ከተማ 3 | ከተማ 4 | ከተማ 5 | ከተማ 6 | ከተማ 7 | ከተማ 8 | ከተማ 9 | ከተማ 10 | ከተማ 11 | ከተማ 12 | ከተማ 13 | ከተማ 14 | ከተማ 15 | ከተማ 16 | ከተማ 17 | ከተማ 18 | ከተማ 19 | ከተማ 20 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8.1 | ለጎብኝዎች የሚደረግ አቀባበል እና ገለፃ (18) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.1.1 | የገለጻ ሰጪዎች በቦታ መገኘት (2) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1) | ገለጻ ሰጪዎች መለያ ባጅ አድርገው በቦታው የተገኙ ከሆነ (2) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2) | ገለጻ ሰጪዎች መለያ ባጅ ሳያደርጉ በቦታው የተገኙ ከሆነ (1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3) | ገለጻ ሰጪዎች በቦታው ያልተገኙ ከሆነ (0) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.1.2 | ገለፃው የፈጀው ጊዜ (በአጭር ጊዜ በቂ መግለጫ መስጠት መቻል) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1) | ገለጻው ከ5 ደቂቃ በታች የፈጀ ከሆነ (1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2) | ገለጻው ከ5-10 ደቂቃ የፈጀ ከሆነ (0.5) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3) | ገለጻው ከ10 ደቂቃ በላይ የፈጀ ከሆነ (0) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.1.3 | የገለፃው ይዘት (Relevance) (1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1) | የዘርፉን ዋና ዋና ፒላሮች ያካተተ ከሆነ (2) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2) | የኢንቨስትመንት፣ የቱሪዝም መስህቦችና ታሪካዊ መረጃዎችን ያካተተ ከሆነ (0.5) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3) | የከተማውን አመሠራረትና እድገት ያካተተ ከሆነ (0.5) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.1.4 | ጎብኚዎች ሲደርሱ በቦታው የነበረው (የነበሩት) የከተማ ተወካዮች ያደረጉት አቀባበል (ሰላምታ፣ ፈገግታ፣ ቅልጥፍና፣ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን)፣ ወዘተ (2) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1) | በቂ አቀባበል የተደረገ ከሆነ (2) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2) | በቂ አቀባበል ያልተደረገ ከሆነ (0) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.1.5 | የድምጽ አጠቃቀሙ ለመደማመጥ እና መግለጫዎችን በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት የሚያስችል እና ሌሎች ተሳታፊዎች የማያውክ ከሆነ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1) | የድምጽ አጠቃቀሙ ከ60 DB በታች ከሆነ (ለመደማመጥ አስቸጋሪ ያለሆነ (10) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2) | የድምጽ አጠቃቀሙ ከ60 DB በላይ ከሆነ (ለመደማመጥ እዳጋች ከሆነ) (0) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.2 | የኤግዚቢሽን አቀራረብ (ከተማው በኤግዚቢሽን መመሪያው የተካተተውን የጥራትና የይዘት መመሪያ መከተሉ) (24) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.2.1 | በውድድሩ የሚቀርቡ መረጃዎች ይዘት (14) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1) | የዘርፉን ዋና ዋና ምሶሶዎች (Pillars) መረጃ ያካተተ (11) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2) | ለኢንቨስትመንት የተዘጋጁ ምቹ ሁኔታዎች መረጃ (1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3) | የቱሪዝም መስህቦችን እና ታሪካዊ መረጃ (1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4) | የነዋሪው ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን መረጃ ((1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.2.2 | የቀረቡ መረጃዎች ጥራት (3) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1) | ጆሖፎችና ቻርቶች በግልጽ የሚነበቡና ሥርዐ ድልዐ የሊለባቸው እና መገለጫዎች ካሏቸው (2) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2) | የመረጃ ጆሖፎችና ቻርቶች ባለቀለም ከሆኑ ( 1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.2.3 | የኤግዚቢሽን የአቀራረብ ቅደም ተከተል (1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3) | የከተማውን አመሠራረትና እድገት መጀመሪያ የተገለፀ ከሆነ (1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4) | የከተማውን አመሠራረትና እድገት ያልተገለጸ ከሆነ (0) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.2.4 | የቻርተሮች፣ ፎቶ-ግራፎችና ፊልሞች አጠቃቀም (3) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1) | ከA3 መጠን ያላነሰ ቻርቶችንና ፎቶ-ግራፎች የተጠቀመ ከሆነ (2) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2) | ከA3 መጠን በታች ቻርቶችንና ፎቶ-ግራፎች የተጠቀመ ከሆነ (1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3) | ዶክመንተሪ ፊልሞች የተጠቀመ ከሆነ (1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4) | ቻርተሮች፣ ፎቶግራፎችና ፊልሞችን ያልተጠቀመ ከሆነ (0) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.2.5 | ኤግዚቢሽኑ የከተማውን የልማት እንቅስቃሴ የኢንቨስትመንት የቱሪዝም መስህቦች በሚገባ ማንፀባረቅ መቻሉ (3) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1) | የኢንቨስትመንት፣ የቱሪዝም እና የባህል፣ ቅርስና ታሪካዊ መስህቦች በሙሉ የቀረቡ ከሆነ (3) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2) | የኢንቨስትመንት መስህቦች ብቻ የቀረቡ ከሆነ (1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3) | የቱሪዝም መስህቦች ብቻ የቀረቡ ከሆነ (1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4) | የባህል፣ የቅርስ እና ታሪካዊ መስህቦች ብቻ የቀረቡ ከሆነ (1) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5) | ምንም አይነት መስህቦች ያልተቀረቡ ከሆነ (0) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.3 | ጥቅም ላይ የዋሉ ራስን የማስተዋወቅ መንገዶች ወይም ጥረቶች (15) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.3.1 | የተዘጋጁ ንግድ ትሪኢቶችና ሴሚናሮችና ጥናታዊ ጉብኝቶች ከቀረቡ (5) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.3.2 | ባህላዊ ስፖርታዊ ሁነቶችን ስፖንሰር ማድረግና ማስተናገድ (5) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.3.3 | ከተማው ራሱን በሚዲያ ያስተዋወቀ ከሆነ (3) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.3.4 | ከተማው ራሱን ዌብሳይት በማዘጋጀት ያስተዋወቀ ከሆነ (2) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.4 | የከተማዋ ልዩ መገለጫዎች (11) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.4.1 | ሎጎ (3) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| (1 | ሎጎ ያለው ከሆነ (3) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| (2 | ሎጎ የሌለው ከሆነ (0) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.4.2 | ሲቲ ብራንድ (ልዩ መገለጫ ስም) (3) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| (1 | ሲቲ ብራንድ ያለው ከሆነ (3) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| (2 | ሲቲ ብራንድ የሌለው ከሆነ (0) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.4.3 | ለጎብኚዎቹ የሚሰጡ የተለያዩ ብሮሸሮች ተዘጋጅተው ስለመቅረባቸው (2) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| (1 | የተለያዩ ብሮሸሮችን ያዘጋጀ ከሆነ (2) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| (2 | የተለያዩ ብሮሸሮች ያላዘጋጀ ከሆነ (0) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8.4.4 | ለኤግዚቢሽኑ ድምቀት የሚሰጡ ባህላዊ እሴቶች (3) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| (1 | ባህላዊ እሴቶችን ያቀረበ ከሆነ (3) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| (2 | ባህላዊ እሴቶች ያለቀረበ ከሆነ (0) | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

| | |
|---|---|
| 8.5 | አዲስ የፈጠራ ውጤት (7) |
| 8.5.1 | የጥ/አ/ኢ/ልማት የሚያፋጥን ግኝት (3) |
| (1 | ግኝቱ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከሆነ (3) |
| (2 | ግኝቱ በሌሎች የከተማ ልማት ዘርፍ ዘርፎች ከሆነ (1) |
| (3 | ግኝት ምንም ያላቀረበ ወይም ከከተማ ልማት ዘርፍ ውጭ የቀረበ ከሆነ (0) |
| 8.5.2 | ለፈጠራ ውጤት እውቅና ለሚመለከተው አካል የተሰጠ ከሆነ (2) |
| (1 | ፈጠራው በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ሆኖ የፈጠራ ውጤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የተሰጠው እና በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጠው ከሆነ (2) |
| (2 | ፈጠራው በሌሎች ዘርፍ ሆኖ የፈጠራ ውጤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የተሰጠው እና በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጠው ከሆነ (1) |
| 8.5.3 | የፈጠራ ሥራው የጥሬ ዕቃ አጠቃቀም (2) |
| (1 | ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ጥሬ እቃ የተጠቀመ ከሆነ (2) |
| (2 | የሀገር ውስጥ እና የውጭ ጥሬ እቃ የተጠቀመ ከሆነ (1) |
| (3 | ሙሉ በሙሉ ከውጭ ጥሬ እቃ የተጠቀመ ከሆነ (0) |
| 8.6 | ከተሞች ኢንቨስተሮችን፣ ቱሪስቶችን ለመሳብ እና ገቢያቸውን ለማሳደግና ለመጠቀም የተደረገ ጥረት (25) |
| 8.6.1. | የተዘጋጁ የኢንቨስትመንት አማራጮች፣ ዝግጅ የሆነ መሬትና መሰረተ-ልማት (8) |
| (1 | በጥናት መረጃ የተደገፈ የኢንቨስትመንት አማራጭ መቅረብ (3) |
| (2 | በጥናት መረጃ የተደገፈ ዝግጁ የሆነ መሬት እና መሰረተ-ልማቶች መሟላታቸውን የሚያመላክት መረጃ መቅረብ(3) |
| (3 | በጥናት መረጃ ያልተደገፉ የኢንቨስትመንት አማራጮች እና ዝግጅ የሆነ የመሬት አቅርቦትና መሰረተ-ልማት ስለመቅረባቸው(2) |
| 8.6.2 | ቱሪስቶች ለመሳብ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች (የሚቀርቡ መረጃዎች በብሮሸር) |
| (1 | መስህቦችን በመገናኛ ብዙኃን (በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ ወይም በኢንተርኔት) ለማስተዋወቅ የተደረገ ጥረት (3) |
| (2 | መስህቦችን በመጽሄትና በጋዜጣ ለማስተዋወቅ የተደረገ ጥረት (2) |
| (3 | መስህቦችን በብሮሸርና በራሪ ወረቀት ለማስተዋወቅ የተደረገ ጥረት (2) |
| 8.6.3 | ከሀገር ውጪ ያሉ የከተማ ነዋሪዎችን (ዳያስፖራ) ተሳትፎ ለማሳደግ የተደረገ ጥረት (5) |
| (1 | ለዲያስፖራው ኮሚኒቲ በከተማው እንዲሳተፍ ልዩ ማበረታቻ መኖሩ (3) |
| (2 | የኢንቨስትመንት አማራጮችን በተለያዩ ሚዲያዎች እንዲሁም በመድረክ ለዲያስፖራው ኮሚኒቲ ለማስተዋወቅ የተደረገ ጥረት (2) |
| 8.6.4 | በራስ አቅም ገቢ ለማሳደግ የተዘጋጁ ፕሮጀክቶችና የተቀየሱ አማራጮች፣ የተፈጠረ ገቢ ስለመቀረቡ (5) |
| (1 | ከተሞች ገቢያቸውን ለማሳደግ የተዘጋጁ ፕሮጀክቶችና የተገኘ ገቢ (3) |
| (2 | ከተሞች ገቢያቸውን ለመጠቀም የተደረገ ጥረትና የተገኘ ውጤት (2) |
| | አጠቃላይ ድምር (ከ100) |

## አባሪ 2፦ በውድድሩ ሂደት በየዕለቱ የቃለ ጉባኤ መያዣ ቅጽ

ቃለ - ጉባኤ ቁጥር ______________

የስብሰባ ቦታ ______________________________

ስብሰባው የተካሄደበት ቀንና ሰዓት ______________________________

በስብሰባው የተገኙ ዳኞች ዝርዝር

1. ______________________
2. ______________________
3. ______________________
4. ______________________

አጀንዳዎች

1. በዕለቱ የተመዘኑ ከተሞች ብዛት____________________
2. በዕለቱ የታዩ ጠንካራ ጎኖችና ክፍተቶች
   - በተመዛኝ ከተሞች በኩል፣

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

   - በመዛኝ ዳኞች በኩል፣

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

   - ሌሎች፣

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

3. ለቀጣይ ምዘና የተቀመጡ አቅጣጫዎች

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

## አባሪ 3፡- የውድድር ማጠቃለያ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

1. መግቢያ
2. ዓላማ
3. በውድድሩ የታዩ ጠንከራ ጎኖችና ክፍተቶች፣
4. ለቀጣይ መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች

የተወዳደሪ ከተሞች ውጤት ማሳወቂያ ቅጽ

| ተ.ቁ | የተወዳደሪ ከተማ ስም | ክልል | ውጤት | ደረጃ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

| ተ.ቁ | የዳኞች ሙሉ ስም | ኃላፊነት | ፊርማ | ቀ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |
| 5 | | | | |